## ለሞት በተደረገ የሕይወት መድን ፖሊሲ ተጠቃሚውን ለይቶ ስለማስታወቅ

በግርማ ወ/ሥላሴ*

ማንኛውም ሰው ለሕይወቱ የኢንሹራንስ ውል ሲዋዋል እንዲሆንለት የሚፈለገው እሱ በሚሞትበት ጊዜ አንድ ሌላ ሰው ከኢንሹራንስ በሚገኘው ገቢ እንዲጠቀም መሆኑ ግልፅ ነው። የሕግ ሊቃውንቶችን ከረዥም ጊዜ ጀምሮ እያጨቃጨቀ ያለው ጥያቄ ግን "የማሕበረሰቡ ፍላጎት ኢንሹራንስ በተዋዋለው ሰው ላይ ተፅዕኖ በማድረግ በሕግ አካማይነት ቢያንስ ቢያንስ የእሱ ባለቤትና ልጆች የኢንሹራንሱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረግ አለበት ወይስ ተዋዋዩ ሙሉ ነፃነት ተሰጥቶት በራሱ ነፃ ምርጫ ተጠቃሚውን መወሰን አለበት?" የሚለው ነው።

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች በዚህ ጥያቄ ላይ በአቋም ተለያይተው ይገኛሉ።** ለፍርድ ቤቶች በቀረቡ ብዙ ጉዳዮች ላይ ተዋዋዮች በሞት ጊዜ ተጠቃሚ የሚሆኑትን ሰዎች ከቅርብ ቤተሰባቸው ውጪ አድርገዋል። ኢንሹራንስ የገባው ሰው በሚሞትበት ጊዜም ክፍያ የሚጠይቁት በፖሊሲው ላይ የተመለከቱት ተጠቃሚዎች ብቻ ሳይሆኑ የንግድ ሕግ ቁጥር 701/2/ን መሠረት በማድረግ የተዋዋዩ ባል ወይም ሚስትና ልጆችም ጭምር ናቸው። በፍርድ ቤቶች ዘንድ የተነሳው አከራካሪ ነጥብም የተጠቀሰው ሕግ የተዋዋዩ ባል ወይም ሚስትና ልጆች በፖሊሲው ላይ ባይጠቀሱና ሌላ ሦስተኛ ሰው በብቸኛ ተጠቃሚነት በግልፅ ቢጠቀስ ከሚገኘው ገንዘብ ማግኘት አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚል ነበር።

በተጠቀሰው የንግድ ሕግ ቁ. 701/1/ ላይ በመመሥረትም የከፍተኛው ፍ/ቤት አንድ ችሎት ኢንሹራንስ የገባው ሰው ከባል ወይም ሚስቱና ልጆቹ ውጪ የሆነ ሰውን ጨምሮ የራሱን ተጠቃሚዎች ሊጠቅስ እንደሚችል ይፈቅዳል።

---

* ፀሐፊው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ት/ቤት ረዳት ፕሮፌሰር ነበሩ።

** በዚህ የሕግ መጽሄት ላይ የወጡትን የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ይመለከቷል። (አዘጋጁ)

በሕይወት መድን ውል ተጠቃሚን ስለመሰየም

ቁጥር 701/1/ን ከንዑስ ቁ. /2/ ጋር አጣምሮ በማንበብ ግን ፍ/ቤቱ ምንም እንኳን በተዋዋዩ በተጠቃሚነት ባይጠቀሱም ባል ወይም ሚስትና ልጆች በማንኛውም ለሞት ጊዜ የሚደረግ የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎች እንደሆኑ ይገመታል ከሚል ማጠቃለያ ላይ ደርሰዋል። ስለዚህ፣ በዚህ ፍ/ቤት መሠረት ኢንሹራንስ የገባው ሰው እናቱን እንደብቸኛ ተጠቃሚ አድርጎ ቢጠቀስም ሴትዮዋ ከኢንሹራንሱ የሚገኘውን ገንዘብ ከሟቹ ባል ወይም ሚስትና ልጆች /እንዲሁም ከሌሎች "ወራሾች" እንደ ፈረንሳይኛው ሕግ አባባል/ ጋር መካፈል ይኖርባታል ማለት ነው።

በግልፅ እንደሚታየው ይህ ትርጓሜ የሚከተለው ተጠቃሚው ማን መሆን አለበት የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ለተዋዋዩ ገደብየለሽ ሥልጣን መስጠትን የሚቃወመውን የአስተሳሰብ መሥመር ነው። ይህንንም አቋም የሚደግፉ ብዙ መከራከሪያ ሃሳቦች አሉ።

መጀመሪያ ነገር፣ ተዋዋዩ አብዛኛውን ጊዜ ብቸኛው የገቢ ምንጭ ነው። በመሆኑም እሱ ቢሞት ቤተሰቡ ሊኖር የሚችልበትን ነገር የማዘጋጀት ግዴታ አለበት። የሚወረስ ንብረት ቢኖርም እንኳን የማጣራቱ ሂደት በአብዛኛው በጣም ረዢም ጉዳይ መሆኑ የቤተሰብ እንገብጋቢ ችግሮችን ወዲያውኑ ለማስወገድ አያስችልም። በሌላ በኩል ደግሞ የኢንሹራንስ ክፍያዎችን በተነፃፃሪ መልኩ በጥሬ ገንዘብ ለማግኘት ቀላል እንደሚል ይታሰባል።

ሌላው የመከራከሪያ ሃሳብ የጋራ ሀብትን ለመጠበቅ ከመፈለግ ጋር የተያያዘ ነው። ምክንያቱም ከሕይወት ኢንሹራንስ የሚገኝ ገቢ ሟቹ ትቶት ከሚያልፈው ጠቅላላ ሀብት ሆኖ ስለማይቆጠርና በውርስ ሕጎችም የሚታይ ባለመሆኑ ከባል ወይም ከሚስትና ከልጆች ውጪ የሆነውን ሰው ለመጥቀም የሚደረግ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ሊወረስ ከሚችለው ሀብት /estate/ ከፍተኛ መጠን ያለውን ገንዘብ ለማግለል በመሣሪያነት ሊያገለግል ስለሚችል ነው።

ሦስተኛ፣ ተጠቃሚ ሰው መጥቀሱ በተለይም የጠቅላላ ሀብቱ ክፍል ቢሆን ኖሮ ግማሹን ሊያገኝ ይችል የነበረውን በሕይወት ያለውን የሟች ባል ወይም ሚስት በከፍተኛ ደረጃ ሊጎዳ ይችላል። መስተዋል ያለበት ሌላው ጉዳይ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ተዋዋዩ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያደርጋቸው ክፍያዎች /premiums/ የባልና የሚስቱ የጋራ ንብረት ከሆነው ከገቢው ላይ መሆኑ ነው።

ስለዚህ ባልና ወይም ሚስትንና ልጆችን፣ የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎች ተብለው ባይጠቀሱም እንኳን፣ ሕግ ተጠቃሚዎች አድርጎ ይህን መሠረታዊ ጥቅማቸውን መጠበቅ ስሜት የሚሰጥ አሠራር ይሆናል። በተጠቀሰው የከፍተኛ ፍ/ቤት ችሎት አስተያየትም የኢትዮጵያ የሕይወት ኢንሹራንስ ሕግ በነዚህ ጉዳዮች ላይ የተመሠረተ ነው።

አንድ የጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎት ግን በነዚህ የመከራከሪያ ሃሣቦች አላመነም። ይህ ፍርድ ቤት ያለው ኢንሹራንስ የገባው ሰው በንግድ ሕግ ቁ. 701/1/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የጠቀሰው ተጠቃሚ በሚኖርበት ጊዜ ይህ ተጠቃሚ ከኢንሹራንሱ የሚገኘውን ገቢ በሙሉ መውሰድ አለበት ነው።

ወደ ቁ. 701/2/ ትርጓሜ በመመለስም ባል ወይም ሚስትና ልጆች የኢንሹራንስ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችሉ የነበረው ተዋዋዩ ማንንም ሰው በተጠቃሚነት ባይጠቅስ ኖሮ ብቻ ነበር በማለት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ወስኖአል።

በአጠቃላይም ሁለቱ ፍርድ ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተቃርነዋል። እንደ መጀመሪያው ውሣኔ ንዑስ ቁ./1/ እና /2/ ተደጋጋፊ ናቸው። በርግጥ አንድ ሌላ ሦስተኛ ሰው በተጠቃሚነት ሊጠቀስ ይችላል፣ ግን ምንም እንኳን በተጠቃሚነት ባይጠቀሱም የሚያገኙትን ጥቅም ከባል ወይም ከሚስትና ከልጆቹ ጋር መካፈል አለበት።

እንደ ሁለተኛው ውሣኔ አባባል ግን የተዋዋዩ ፍላጎት ገዥ ነው። በመሆኑም ማንኛውም በእሱ እንደተጠቃሚ የተጠቀሰ ሁሉ ከፖሊሲው የሚገኘውን ጥቅም በሙሉ ያገኛል። ባል ወይም ሚስትና ልጆች ሊያገኙ የሚችሉት ተዋዋዩ ተጠቃሚን ሳይጠቅስ የሞተ እንደሆነ ብቻ ነው።

እነዚህ የተለያዩ የሁለት ፍ/ቤቶች ውሣኔዎችም ኢንሹራንስ ገቢዎችንም ሆነ ኢንሹራንስ ሰጪዎችን ፍፁም ወጥንቅጥ የወጣ ሁኔታ ውስጥ ጥለዋቸዋል። ይህም የስታሬ ዲሲስ /በአንድ ጉዳይ ላይ አንድ የበላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሌሎች የበታች ፍ/ቤቶች እንዲከተሉት የሚገደዱበት/ ሥርዓት በእኛ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ባለመኖሩ ምክንያት ተባብሷል።

ይህ ሁኔታም እላይ የተጠቀሰው ጉዳይ በጠቅላይ ፍ/ቤት የተሻረ አንድ ተራ የሆነ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ላለመሆኑ አንድ ምክንያት ነው። ያ ቢሆን ኖሮ ጉዳዩ በጣም ቀላል ይሆን ነበር። ይህ ግን አንድ የበታች ፍ/ቤት በተመሳሳይ ጉዳይ በሌላ የበላይ ፍ/ቤት የተወሰነን ሁኔታ በግልፅ ውድቅ ያደረገበት ሁኔታ ነው። ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀደም ሲል የጠቅላይ ፍ/ቤት በተመሳሳይ ጭብጦች ላይ በተመሠረተ ጉዳይ ላይ የሰጠውን ፍርድ የተመለከተው መሆኑን ገልጿል። የበታች ፍ/ቤቱ ግን የጠቅላይ ፍ/ቤት ለንግድ ሕግ ቁ. 701 የሰጠውን ትርጓሜ እንደማይቀበልና ይህ የበላይ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ጋር ለመስማማትም በምንም ዓይነት ደረጃ እንደማይገደድ ገልጿል። ስለዚህ ተቃራኒ ማጠቃለያ ላይ የደረሰው እያወቀ ነበር ማለት ነው። በግልፅ እንደሚታየው እነዚህ ጉዳዮች የእኛ የሕግ ሥርዓት ለቀደምት የፍርድ ቤት ውሣኔዎች /precedents/ ምን ዓይነት ቦታ መስጠት አለበት የሚል ወቅታዊ ጥያቄ ሊያስነሣ ይችላል። ሆኖም ግን ይህ ጥያቄ የዚህ ፅሁፍ ዋና ዓላማ አይደለም።

እዚህ ላይ የምናተኩረው የተጠቀሱት ሁለት ውሣኔዎች የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ አወሳሰንን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ የሆነ አቋም የያዙ የተለያዩ የአስተሳሰብ መሥመሮች የሚከተሉ በመሆናቸው ላይ ነው። ሁለቱ አመለካከቶችም በተራቸው የሚያንፀባርቁት የተለያዩ ማሕበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ የዕድገት ደረጃዎችን ነው። ስለዚህ በሥርዓተ ሕጋችን ዕድገት ውስጥ አሁን መታየት ያለበት ጥያቄ ከእነዚህ አመለካከቶች መካከል የዛሬይቱ ኢትዮጵያን ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ የሚያገለግለው የትኛው ነው የሚለው ነው።

የአንድን ሕግ ትርጉም ሙሉ በሙሉ ለመረዳት አንዱና በጣም ጠቃሚው መንገድ የሕጉን ታሪካዊ ዕድገት ማጥናት ነው። ለዚህም የመጀመሪያ ረቂቆች፣ ቀጣይ ለውጦች፣ የአርቃቂ ኮሚሽን ቃለ ጉባኤዎች፣ እንዲሁም የፓርላማ ክርክሮች በጣም ጠቃሚ መገልገያዎች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ላይ በቀላሉ የምናገኘውና በመጠኑም ሊረዳ የሚችለው የዚህን ሕግ ረቂቅ ብቻ ነው።

ያም ሆኖ በንግድ ሕግ ቁ. 701 ላይ ፕሮፌሰር ዥፍሬ[1] የሰጡት ነገር እራሱ በሚያፀፅት ሁኔታ በጣም ጥቂት ነው። ነገር ግን በአንድ ጠቃሚ ዐረፍተ ነገር አማካኝነት ይህ ሕግ ምን እንዲል እንደተፈለገ ሊያሳይ የሚችል ፍንጭ ሰጥተውናል። አርቃቂውም ሲፅፉ "የሕይወት መድን ተጠቃሚ አወሳሰንን በተመለከተ በጣም ልቅ /the most liberal/ የሆነ መፍትሄ አስገብቻለሁ" ብለዋል። እንደመጥፎ አጋጣሚ ሆኖ ግን "በጣም ልቅ በሚሉበት ጊዜ ምን ማለታቸው እንደሆነ ምንም አልተናገሩም። በመሆኑም አንድ ሰው ለሞት ጊዜ ስሚደረግ ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ማን መሆን አለበት የሚለውን ለመወሰን "ፖሊሲ" ሲገባ ምን እንደሆነ ለማወቅ ከዚህ ራቅ አድርጎ መመልከት አለበት።

በዚህ ረቂቅ ውስጥ ዥፍሬ "ልቅ" የሚለውን ቃል በሌሎች ብዙ አጋጣሚዎች ሁሉ ተጠቅመውበታል። ለምሳሌ የሌሎች ጥቂት አገሮችን ሕጎች በመጥቀስ የአንድ የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ተዋዋይ ሕይወቱን በራሱ በማጥፋቱ ምክንያት ትክክለኛነቱን እያጣም በማለት ተናግረዋል። ይህ ዓይነቱን አቋም ከሚገባው በላይ "ልቅ" ይሉትና በኢትዮጵያው ረቂቅ ሕግ ላይ ተቃራኒ መሥመር ተከትለዋል። እነዚያ አገሮች ሰውየው ሕይወቱን በራሱ ቢያጠፋም እንኳን የእሱን ፍላጎት ውጤት በመስጠት መቀበል መምረጣቸውንና ዥፍሬ ይህን አቋም "ልቅ" የሚል ቃል በመጠቀም ከገለፁት በመነሣት ስለ ቁ. 701 ሲናገሩም ቃሉን መጠቀማቸው ተመሳሳይ ሀሣብ፣ ማለትም የተዋዋዩን ፍላጎት ማስቀደምን፣ ለማስተላለፍ መሆን አለበት ወደሚል ማጠቃለያ ያመራል።

---

[1] የመጀመሪያው የንግድ ሕግ አርቃቂ የነበሩት ፕሮፌሰር አስካሬ የሞቱት ገና ሥራው ከማለቁ በፊት ነው። በመሆኑም ፕሮፌሰር ዥፍሬ ወደ መጨረሻ አካባቢ የአርቃቂነት ሥራውን ስለተረከቡ በኢንሹራንስ ላይ ላለው የማርቀቅ ሥራ ኃላፊው እርሳቸው ነበሩ።

ይህ የክርክር መሥመር በተለይም ሌሎች አገሮች "ልቅ" የሚሉትን ቃል በምን መልክ እንደሚጠቀሙበት በመጥቀስ የበለጠ ሊጠናከር ይችላል። በኢትዮጵያ ተመሳሳዩ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ያሳደረው የፈረንሣይ የሕይወት ኢንሹራንስ ሕግ የተለየ ተሞክሮ አለው።[2]

ለልቅነት ትርጉም የፈረንሣይን ሕግ የምንፈልግበት ሌላው ምክንያት ደግሞ የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚን፣ በሞት ጊዜ፣ ስለመወሰን ጉዳይ በጣም "ልቅ" በመባል የሚታወቀው ይህ የፈረንሣይ ሕግ በመሆኑ ነው። እንደ አንድ ፀሐፊ አባባል "የተጠቃሚውን ማንነት መግለፅን በሚመለከት የፈረንሣይ ሕግ ደንቦች /የ1930 ሕግ ቁጥር 63/ ከመጠን በላይ በፊና ልቅ ናቸው። ይህም መድን የገባው ሰው ያቀደውን ዓላማ በላቀ ሁኔታ ለመወጣት እንዲችል ለማድረግ ሲባል ነው።"[3]

ስለዚህ ቢያንስ ቢያንስ በፈረንሣይ የሕግ ሊቃውንት አመለካከት በአብዛኛው የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚን በተመለከተ "ልቅ" አቋም በመባል የሚታወቀው ፖሊሲውን ለፈረመው ሰው በጣም ዝቅተኛ ገደብ ያለበትን ነፃነት የሚሰጠውን አቋም ነው። በዚህ መሠረት አንድ ሰው የፈረንሣይ የሕግ ሊቅ የሆኑት ዥ ፍሬ "በጣም ልቅ የሆነውን መፍትሄ" መርጫለሁ ካሉት በመነሣት፣ ማለት የፈለጉት ተዋዋዩ የፖሊሲው ተጠቃሚ ማን መሆን እንዳለበት ለመምረጥ ከፍተኛ ነፃነት ሊኖረው ይገባል ነው፣ ወደሚል ምክንያታዊ የሆነ ማጠቃለያ ሊደርስ ይችላል። ይህም ግብ የተገኘው በንዑስ ቁ/1/

2 ዥ ፍሬ ፊላቸው "ብዙ ዘመናዊ ሕጎችን በተለይም የጁላይ 13፣ 1930ውን የፈረንሣይ ሕግ ... ተመልክቻለሁ" ብለዋል፣ ፒተር ዊንሸፕ ባክግራውንድ ዶኩመንትስ ኦቭ ዘ ኢትዮጵያ ኮመርሻል ኮድ ኦፍ 1960 (አዲስ አበባ፣ ሕግ ፋኩልቲ አ.አ.ዩ አ.አ.አ 1972) ገጽ 83።

3 ጄላነር እና ጆ ኖርድ /አዘጋጆች/ ላይፍ ኢንሹራንስ ሎ ኢን ኢንተርናሽናል ፐርስፔክቲቭ፣ ሬፖርትስ ፎርም እን ኢንተርናሽናል ኮሎኪየም /ስቶኮልም፣ 1969/ ገጽ 29።

በሚያምታታ ሁኔታ በተገለፀውና "ለሞት የሚደረግ ኢንሹራንስ ለአንድ የተለዩ ተጠቃሚ ጥቅም ሊደረግ ይችላል" በሚለው ነው።

በአርቃቂው ረቂቅ አውሮፓውያን ተጠቃሚን በመወሰን ረገድ በሚከተሉት "ለቀቅ"፣ "ለበብ" ያለ ፖሊሲ ላይ በመመርኮዝ ቁ. 701 የተመሠረተበትን ፖሊሲ በዚህ ሁኔታ ካስቀመጥን በኋላ የሚቀረን ንዑስ ቁ /2/ ከንዑስ ቁ. /1/ ጋር የማስታረቁ ሥራ ነው።

ለመነሻም ያህል፣ ንዑስ ቁ. /1/ አርቃቂው ከነለፀት ግባቸው ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጣጣም ነው የሚል አንድ ክርክር አለ። ይህ ሕግ የሕጉ አርቃቂ የተጠቃሚ አወሳሰን በተመለከተ የሚነሳውን ነቀፋ "በጣም ልቅ" በሆነ መንገድ ለማቃለል የነበራቸውን ፍላጎት የገለፁበት ሕግ ነው። "በጣም ልቅ" የሚለው አባባልም በተራው፣ ተዋዋዩ ተጠቃሚውን ለመምረጥ ያለው ነፃነት በጣም ከፍተኛ /በጣም ትንሽ ገደብ ብቻ ያለበት/ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

ወደ ሁለተኛው ንዑስ ቁጥር ስንመለስ ደግሞ አርቃቂው ሁለት ተቃራኒ ሐሳቦች በአንድ ቁጥር ውስጥ አጠቃለዋል ብሎ መውሰድ ከሕግ ማርቀቅ መሠረታዊ መርሆች ጋር መቃረን ይሆናል። በሌላ አባባል፣ በንዑስ ቁ. /2/ የተገለፀው በንዑስ ቁ. /1/ የተገኘውን የአርቃቂውን ግብ በሚያጠፋ መንገድ መተርጎም የለበትም ማለት ነው።

ሆኖም ግን ይህ ዓይነቱ አለመጣጣም በማንኛውም ሕግ፣ በተለይም በመጀመሪያው ረቂቅ ሕግ ላይ ከአርቃቂው ውጪ በሆኑ ሰዎች ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ ሊፈጠር የሚችል እንደሆነ መታመን አለበት። እንዲህ ዓይነት ለውጦች ሲደረጉ በሌሎች ሕጎችና ግፋ ቢልም ጠቅላላው ሕግ በተዋቀረበት ፖሊሲ ላይ ምን ዓይነት ችግር ሊያስከትሉ እንደሚችሉ በቂ ትኩረት አይሰጥም። ይህ ሊሆን ከመቻሉ አንፃር ሲታይ፣ ለጊዜውም ቢሆን ንዑስ ቁ. /2/ ንዑስ ቁ. /1/ን ይቃረናል ብንል፣ እንዲሁም ንዑስ ቁ. /2/ በአርቃቂ ከሚሽኙ ወይም በፓርላማው በኋላ የተጨመረ ወይም የተለወጠ ሆኖ ቢገኝ አስገራሚ ይሆናል።

በሕይወት መድን ውል ተጠቃሚን ስለመሰየም

ነገር ግን ሁኔታው እንዲህ እንዳልነበር የሚያሳይ ከሞላ ጎደል አስተማማኝ የሆነ መረጃ አለ። ሞኖሬ በንግድ ሕጉ የኢንሹራንስ ክፍል ላይ ያቀረቡት ረቂቅ በአርቃቂ ኮሚሽን ያለምንም ለውጥ ተቀባይነትን አግኝቷል። በአንድ የአርቃቂ ኮሚሽኑ አባል እንደተፃፈ የሚታመንበትና በረቂቁ የመጀመሪያ ገፅ ላይ ለሞኖሬ የተፃፈው የእጅ ፅሁፍ የሚገልፀው ረቂቁ "ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት እንዳገኘ" ነው።[4]

የመጀመሪያ ረቂቁና የአሁኑ የቁ. 701 ይዘት ሙሉ በሙሉ አንድ መሆናቸው አርቃቂ ኮሚሽኑም ሆነ ፓርላማው በሞኖሬ ረቂቅ ላይ ምንም ለውጥ ያላደረጉ ለመሆናቸው ሌላው ማስረጃ ነው።[5]

<u>የቁ. 701/2/ ትርጉም</u>

የኢትዮጵያን ሕግ የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ አወሳሰን አስመልክቶ ሕግ አውጪው የተመሠረተበትን ፖሊሲ ለማወቅ ጥረት ተደርጓል። ከላይ የተገለፀውን ግብ ለማንፀባረቅ ተብሎ የቀረበው የመጀመሪያ ረቂቅም በየትኛውም ወደ ሕግነት ለመሸጋገር ባለፈባቸው ደረጃዎች ውስጥ ምንም ዓይነት ለውጥ እንዳልተደረገበት አይተናል። በመጨረሻም፣ የቁጥር 701 የመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር የኢንሹራንስ ጥቅም ለማን

4 ፒተር ዊንሸፕ ከተመሳሳይ ማጠቃለያ ላይ ደርሰዋል። ሲፅፉም "አርቃቂ ኮሚሽኑ የፕሮፌሰር ሞኖሬን ረቂቅ ያለ ምንም ማሻሻያ የተቀበለው ይመስላል። በሕግ ፋክልቲ /አ.አ ዩኒቨርሲቲ/ መፃሕፍት ቤት /አርካይቭስ/ ውስጥ የሚገኘው የረቂቁ ቅጅ ከመጀመሪያው ገፅ የላይኛው ጠርዝ ላይ የተፃፈ እንደሆነ /ማቲር ፖርዳኅስ በተባለ የንዑስ ኮሚሽኑ አባል በሆነ ሰው የእጅ ጽሁፍ የተፃፈ እንደሆነ የሚታሰብ/ ረቂቁ ያለምንም ማሻሻያ ተቀባይነት እንዳገኘ የሚገልጽ ጽሁፍ ይገኛል" ብለዋል። ፒተር ዊንሸፕ፣ በማስታወሻ ቁ. 2 የተጠቀሰው መጽሀፍ ገጽ 6.

5 ብቸኛው አለመጣጣም የሚታየው እንግሊዝኛ አስተርጓሚ በሆነው በመጀመሪያው ረቂቅ የሚገኘውና "ወራሽ" የሚለው ቃል ከአማርኛውና ከእንግሊዝኛው አለመካተቱ ነው። እዚህ ላይ እንዲህ ያለ ልዩነት በረቂቁ ላይ በተደረገ ማሻሻያ ምክንያት ነው ሊባል አይችልም። ምክንያቱም የንግድ ሕጉ የፈረንሳይኛው ቅጅ እስከአሁን ድረስ ይህን ቃል እንደያዘ የሚገኝ ነው።

መስጠት እንዳለበት የመወሰን ሙሉ ነፃነት ለተዋዋዩ ስለሚሰጠው ከተገለፀው የሕግ አውጪ ፖሊሲ ጋር በሙሉ እንደሚስማማ ግልፅ ነው።

ስለዚህ 701 /2/ን፣ ልክ እንደኛው ፍ/ቤት እንዳደረገው ሁሉ ተዋዋዩ ለሞት ጊዜ በገባው የሕይወት ኢንሹራንስ ላይ ሌላ ሦስተኛ ሰው በብቸኛ ተጠቃሚነት በግልፅ ቢጠቅስም እንኳን የተዋዋዩ ባል ወይም ሚስትና ልጆች በማንኛውም ጊዜ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ ብሎ መተርጎሙ ሕጉ የተመሠረተበትን መሠረታዊ ፖሊሲ ከመቃወሙም ባሻገር በቀዳሚው ንዑስ ቁጥር የተደረሰበትን ግብ የሚያጠፋ ይሆናል። በዚህም ምክንያት ብቻ የተጠቀሰው ትርጓሜ ውድቅ መደረግ አለበት።

ያም ሆኖ ግን ይህን ማጠቃለያ በመደገፍ ሌሎች ክርክሮችም ሊነሱ ይችላሉ። ከተገለፀው "ልቅነት" ጋር በሚጣጣም መልኩ ሕጉ ለኢንሹራንስ ውል ተዋዋዩ በውሉ ውስጥ ተለይቶ የተጠቀሰው ተጠቃሚ ጥቅሙን እቀበላለሁ እስካላለ ድረስ ተጠቃሚውን መለወጥ የሚያስችል ሥልጣን ሰጥቶታል /ቁ. 703/2/። በሌላ ጎኑ ግን ባል ወይም ሚስትና ልጆች ከተዋዋዩ ፍላጎት ውጪ በሆነ ሁኔታና በሕጉ ትዕዛዝ ብቻ ተጠቃሚዎች ተብለው የሚቆጠሩ ከሆኑ ተዋዋዩ ተጠቃሚውን መቀየር እንደሚችል ሥልጣን መስጠቱ ትርጉም የለሽ በሆነ ነበር። በድጋሚ ለመግለፅም ቁጥር 701/2/ን ወደ እንደዚህ ዓይነት ተቃርኖ በሚያመራ መልኩ መተርጎም ተቀባይነት አይኖረውም።

ከዚህ በላይ የተገለፀው ትርጓሜ የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ በዘመናዊ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚጫወተውን ዘመናዊ የመሣሪያነት ጠቀሜታ ዋጋ የሚያሳጣው ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ በአደጉ አገሮች ውስጥ አንድ ሰው ለአበዳሪው ጥቅም የኢንሹራንስ ውል መግባትና ውሉንም ለዚህ ተጠቃሚ አንድ ሌላ ግዴታን ለመፈፀም እንደዋስትና መውሰድ የተለመደ ነገር ሆኗል።

ይህ ተግባርም ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ መጠነኛ ጊዜያትን አስቆጥሯል። ለምሳሌ ያህልም ቤት ለመሥራት ከቤቶችና ገንዘብ ቁጠባ ባንክ /Morgage Bank/ ገንዘብ የተበደሩ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን መውሰድ ይቻላል። ብድሩን ለማግኘት በቅድመ ሁኔታነት ባንኩን ተጠቃሚ ያደረገ የኢንሹራንስ ውል ውስጥ እያንዳንዳቸው መግባት ነበረባቸው።

በሕይወት መድን ውል ተጠቃሚን ስለመሰየም

የኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ሕግ፥ እንደ አንድ ዘመናዊ የሕግ ክፍልነቱ፥ ይህን የሕይወት ኢንሹራንስ ጥቅም ያውቃል። ለምሳሌ ቁ. 692/1/ ኢንሹራንስ ሰጪው ኢንሹራንስ የገባው ሰው በሚሞትበት ጊዜ" ኢንሹራንስ ከገባው ሰው መብት ላላቸው ሰዎች ...” የተወሰነ ገንዘብ /ካፒታል/ ለመስጠት ግዴታ ውስጥ ሊገባ የሚችልበትን ሁኔታ ያሳያል።

ቁጥር 697 ደግሞ የኢንሹራንስን ውል መያዣ ማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ በግልፅ በመፍቀድ ይህን ጉዳይ የበለጠ ያብራራዋል።

ቁ701(2)ን የተዋዋዩን ነፃ ፍላጎት በሚገድብ ሁኔታ መተርጎም ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት የሕግ ቁጥሮች መንፈስ ጋር ከመፃረሩም በተጨማሪ አስገራሚ ውጤት ሊያስከትል ይችላል። ለምሳሌ የብድር ባንክ ብቸኛው የኢንሹራንሱ ተጠቃሚ ሆኖ በሚጠቀስበት ጊዜ ከኢንሹራንሱ የሚገኘውን ገቢ የተዋዋዩ ባል ወይም ሚስትና ልጆቹ ተካፋይ ሊሆኑ ነው፤ ይህም የውሉን ዓላማ በማጥፋት ይህን የሕይወት ኢንሹራንስን መያዣ በማድረግ የተገባውን የብድር ውል ዋጋ ያሳጣዋል ማለት ነው።

በላይኛው የመከራከሪያ ሃሳቦች ላይ በመመሥረትም፥ ቁ. 701/2/ን የኢንሹራንስ ውል የገባው ሰው አንድ ሌላ ሰውን ብቸኛ ተጠቃሚነት ጠቅሶ በሚሞትበት ጊዜም ቢሆን እንኳን የሟች ባል ወይም ሚስትና ልጆች ከሚገኘው ገቢ የተወሰነውን ክፍል ማግኘት አለባቸው ብሎ መተርጎም ሕጉ የተመሠረተበትን ፖሊሲና ብዙ ሌሎች መሠረታዊ ሕጎችን ስለሚፃረር ውድቅ መሆን ያለበት ነው ለማለት ያስገድዳል።

ይህ ከተባለ በኋላ መታየት ያለበት ለዚሁ ሕግ ሁለተኛው ፍ/ቤት የሰጠው አማራጭ ትርጉም ነው። እዚህ ላይ ፍ/ቤቱ በቁ. 701/2/ መሠረት ኢንሹራንስ የገባው ሰው ከባል ወይም ከሚስትና ከልጆች ውጪ የሆነ ተጠቃሚ ሊጠቅስ እንደሚችል ዕውቅና ይሰጥና፥ ይህንንም ሊያደርግ የተጠቀሰው ተጠቃሚ ከፖሊሲው የሚገኘውን ገንዘብ በሙሉ ሊወስድ እንደሚችል ይናገራል።

ሁለተኛውን ንዑስ ቁጥር በተመለከተ ፍ/ቤቱ የወሰደው አቋም ኢንሹራንስ የገባው ሰው በተጠያቂነት ሳይጠቅሳቸው በሚሞትበት ጊዜም እንኳን በሕጉ ብቻ ባል ወይም ሚስትና ልጆች የፖሊሲው ተጠቃሚዎች ይሆናሉ የሚለው ነው።

ከዚያም ፍ/ቤቱ እነዚህን ሁለት ተቃራኒ አቋሞች ማስታረቅ ነበረበት። ይህንንም ሥራ ያከናወነው በተጠያቂነት ያልተጠቀሱ የተዋዋዩ ባል ወይም ሚስትና ልጆች የኢንሹራንሱን ጥቅም ሊያገኙ የሚችሉት በመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር የተመለከተው ሁኔታ ሳይኖር፣ ማለትም ተዋዋዩ የተወሰነ ተጠቃሚ ሳይጠቅስ በሚቀርበት ሁኔታ ብቻ ነው ብሎ በማጠቃለል ነበር። በዚህ አኳኋንም ፍ/ቤቱ ከላይ ከተጠቀሰው የሕግ አወጣጥ ፖሊሲ ጋር በሚጣጣም መንገድ ኢንሹራንስ የገባውን ሰው ፍላጎት የበላይነት ጠብቋል። እስከዚህ ወሰን ድረስም ውሣኔው ትክክል ነው።

ይህ ፀሐፊ ግን ፍርድ ቤቱ ለሕጉ ሁለተኛ ንዑስ ቁጥር ከሰጠው ትርጓሜ አንድ ነጥብ ማንሣት ይፈልጋል። በዚህ ፍ/ቤት አባባል የዚህ ንዑስ ቁጥር ጠቀሜታ ኢንሹራንስ የገባው ሰው ከፖሊሲው የሚገኘው ገንዘብ ወደማን መሄድ እንዳለበት ምንም ሳይናገር በሚሞትበት ጊዜ የተዋዋዩን ባል ወይም ሚስትና ልጆች ተጠቃሚዎች ለማድረግ ነው።

ሆኖም ግን ኢንሹራንስ የገባው ሰው ተጠቃሚውን ሳይወስን የሞተ እንደሆነ ከኢንሹራንሱ የሚገኘው ገንዘብ ወደየት መሄድ እለበት የሚለውን በተመለከተ ሕጉ ፍፁም ግልፅ ነው። የፍትሐብሔር ሕግ /ቁ. 827/ም ሆነ የንግድ ሕግ /ቁ. 705/ ገንዘቡ "የሚከፈለው ኢንሹራንሱን ለተዋዋለው ሰው ወራሽ ነው" በማለት የውርሱ ሀብት ክፍል ያደርጉታል። በዚህ ጉዳይ ላይ የሁለቱ ሕጎች አንድነትና የሚጠቀሙት ቋንቋም የሚያምታታ አለመሆኑ ለትርጉም ቦታ እንደሌለ ያሳያል። በመሆኑም ለንግድ ሕግ ቁ. 701/2/፣ ልክ ከላይ እንደተጠቀሰው ፍ/ቤት ዓይነት እነዚህን ሁለት ሕጎች የሚቃረን ትርጉም መስጠቱ ተቀባይነት የሚያገኝ አይሆንም።

የቁ. 701/2/ ትርጉም ምን መሆን አለበት፣ ዓላማውስ ምን ነበር? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የንዑስ ቁ./1/ እና /2/ን የቃላት አጠቃቀም በጣም ቀረብ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል።

በመጀመሪያው ገፅ ቁጥር ተዋዋዩ የኢንሹራንስ ፖሊሲውን "ተለይቶ ለታወቀ" ተጠቃሚ ጥቅም ሊያደርገው እንደሚችል ሥልጣን ተሰጥቶታል። "ተለይቶ ለታወቀ" ማለት ምን ማለት ነው? በሌላ አባባል ተዋዋዩ ምን ያህል "ውስን" መሆን አለበት? በጣም ብዙ ተዋዋዮች ከተጠቃሚዎቻቸው ጋር ወደፊት ስለሚኖራቸው ግንኙነት ለመተንበይ ካለው አስቸጋሪነት አንፃር ሊለወጥ በማይችል መልኩ መዋዋል ስለማይፈልጉ የዚህ ጥያቄ አስፈላጊነት በጣም ከፍተኛ ይሆናል። እንደ ዕውነቱ ከሆነ በአንዳንድ አገሮች "የተወሰነ" ሰው በስም ተጠቃሚ ሆኖ የሚጠቀሰው በጣም በጥቂቱ ነው።

በዴንማርክ ሕግ ለምሳሌ፣ "ተዋዋዩ ባሏ ወይም ሚስቱ የኢንሹራንሱን ገቢ በሙሉ እንዲወስድ ከፈለገ ተጠቃሚ" ባል ወይም ሚስት" ብሎ በመጥቀስ ማግኘት ይችላል። ስለዚህ ባል ወይም ሚስትን በስም መጥቀስ አያስፈልገውም ማለት ነው። ተዋዋዩ ልጆቹ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ከፈለገ "ልጆች" በሚል የተጠቃሚ አጠቃቀስ /የእያንዳንዳቸውን ስም ሳይጠቅስ/ ሊገልፅ ይችላል።

ሁኔታው እንዲህ ሳለ፣ ተጠቃሚዎችን በመጥቀስ ላይ የጠቅላላ ቃላትን /general terms/ አጠቃቀም የሚቆጣጠር ሕግ የሌለው ማንኛውም የኢንሹራንስ ሕግ የተሟላ ሊሆን አይችልም። ቁ. 701/2/ም በኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ሕግ ውስጥ የተካተተው ይህን ዓላማ ለማሳካት መሆኑ ታምኖበታል።

ይህን ሀሳብ ለማብራራት ተዋዋዩ ፖሊሲው "የተወሰኑ" ተጠቃሚዎችን እንዲጠቅም ለመጥቀስ የሚያስችለውን የቁ. 701/1/ን ይዘት በበለጠ እንመርምር። ምን ያህል የተወሰኑ ወይም የተለየ መሆን አለበት የሚል ጥያቄ ተነስቷል። በተዘዋዋሪ ሊሆን ቢችልም ግን ለዚህ ጥያቄ መልስ ከሁለተኛው ገፅ ቁጥር ማግኘት ይቻላል። በዚያ ሕግ ሥር የተወሰኑ ሰዎች "ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች ተብለው ይቆጠራሉ" /አፅንኦት የታከለበት/። ስለዚህ በዚህ ገፅ ቁጥር ውስጥ "ተለይቶ የታወቀ" የሚለው ቃል መተርጎም ያለበት ተጠቃሚውን በስም እንደመጥቀስ ማለትና ይህንንም አለማድረግ የህጉን ተፈላጊ ነገሮች እንዳለማሟላት ተደርጎ ነው።

ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ብዙ ጠቃሚታዎች እንዳሉት ግልፅ ነው። ጥቅሙ ለማን መስጠት እንዳለበት በፍፁም ርግጠኛነት የወሰኑ ተዋዋዮችን ፍላጎት ይጠብቃል። ሁለተኛ ደግሞ ሰዎች ከተጠቀሱ የተዋዋዩ ፍላጎት የማያጠራጥር ስለሚሆን ተጠቃሚው ማን መሆን እለበት የሚሉ ጭቅጭቆችን እጅግ በጣም ይቀንሳቸዋል፣ ወይም ያጠፋቸዋል።

በሌላ መልኩ ደግሞ ተዋዋዮች ሁሉ እስከዚህ ደረጃ ድረስ ወስነው እንዲያሳውቁ መጥከር ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ሃሳብ አይሆንም። ከፍ ብሎ እንደተገለፀው በብዙ አገሮች ለሞት ጊዜ የሚሆን ኢንሹራንስ ከሚገቡ ሰዎች ውስጥ ተጠቃሚዎቻቸውን በስም የሚገልፁ በጣም ጥቂቶች ብቻ ናቸው።

ነገ ለእነርሱ ምን አዘጋጅቶ እንደሚጠብቃቸው በርግጠኛነት ስለማያውቁ ብዙ ተዋዋዮች ሊሻር የማይችል ውል መፈራረምን አይቀበሉትም። በኢትዮጵያ ሕግ ለምሳሌ "ለአንድ ተለይቶ ለታወቀ ተጠቃሚ የተሰጠ የኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚው እንደሚቀበል መፍቀዱን ካስታወቀ በኋላ ሊሻር አይችልም" /የንግድ ሕግ ቁ. 703/1/፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 1961/1/ንም ተመልከት/፣ ለቤተሰቡ የገንዘብ ዋስትና መስጠት የተመኘና ለዚህም ሲል ለሞት ጊዜ የሚሆን የሕይወት መድን የገባ አንድ ሰውን ወስደ መመልከት የዚህ መሰሉ ውል ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ሙሉ ለሙሉ ሊያስረዳ ይችላል። ሰውየው ሚስቱ የሆነችውን "ታሚማ"ን ተጠቃሚ አድርጎ እንበል። ታሚማም ፖሊሲውን ወዲያውኑ ተቀበለች። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ተፋቱና በየበኩላቸው ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መሠረቱ። በተጨማሪም ተዋዋዩ ከአዲሷ ሚስቱ ብዙ ልጆችን ሊወልድ ከታሚማ ግን ምንም አልወለደም እንበል። የኢንሹራንሱ ገንዘብ ያለምንም እንከን ለታሚማ ይሰጣል፤ የፖሊሲው ዓላማም ከንቱ ይቀራል ማለት ነው፤

ከእንዲህ ዓይነት አጋጣሚ ለመከላከል ነው ብዙ ተዋዋዮች ተጠቃሚውን ሲጠቅሱ "ባለቤቴ" ወይም "ሚስቴ" የሚሉትንና መሰል የአጠቃላይነት ባሕርይ ያላቸውን ቃላት መጠቀምን የሚመርጡት።

6 ሄልነር አላይ በማስታወሻ 3 የተጠቀሰው ገጽ 18፤

7 ይህንኑ መጽሐፍ ገጽ 17 ይመልከቱ፤

በሕይወት መድን ውል ተጠቃሚን ስለመሰየም

ልጆቼ ከሚለው እንዲጠቀሙ የፈለገን ተዋዋይ ደንብ እንመልከት። ውሉን በፈረመበት ጊዜ የተወለዱትን ልጆች ስም ቢፅፍ እነርሱ ብቻ ተጠቃሚ ሊሆኑ ነው፤ ይህም ውሉን ከተዋዋሉ በኋላ የተወለዱትን ጨምሮ ሁሉንም ልጆቹን ለመጥቀም ከፈለገ ከተዋዋይ ፍላጎት ውጪ ይሆናል። ይህ አመለካከትም ብዙ ሰዎች ግለሰቦችን በስም ከመጥቀስ ይልቅ "ልጆች" ወይም "ተወላጆች" እና የመሳሰሉ አጠቃላይነት ያላቸውን ቃላት ለምን እንደሚመርጡ ያሳያል።

ሌላው ተዋዋዮች አዘውትረው የሚጠቀሙበት ቃል "ወራሾች" የሚለው ነው። /ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ይህ ቃል በንግድ ሕግ ቁ. 701/2/ በፈረንሳይኛው መጽሐፍ ቢገኝ በአማርኛውና በእንግሊዝኛው ግን አይገኝም/። ተዋዋዩ ወራሾችን በተጠቃሚነት በስም ከጠቀሱ በልጆች ጉዳይ የተነሣው ጥያቄ እዚህም ተመልሶ ይመጣል።

ስለዚህ ቁ. 701/2/ የሚያገለግለው አጠቃላይ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ተጠቃሚዎች ስለሚጠቀሱበት ሁኔታ እውቅናና ጥበቃ ለመስጠት ነው። በሌላ አባባል ተዋዋዩ "ሚስቴ"፣ "ልጆቼ"፣ "ወራሾቼ" እና የመሳሰሉ ቃላትን መጠቀም ሲመርጥ እነዚህን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ሰዎች "ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም" ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች ተብለው ይቆጠራሉ ማለት ነው።

በነገራችን ላይ ይህ አቋም ከፈረንሳይ ሕግ አቋም ጋር አብሮ ይሄዳል። በ ኤ ቢሰን አባባል።

"በርግጥ ተጠቃሚውን በስም ከመጥቀስ /በትክክል/ የሚያግድ ምንም ነገር የለም። በዚህም መንገድ ተጠቃሚው በግልፅ ይታወቃል። ሆኖም መድን የገባው ሰው ገንዘቡ በሚከፈልበት ጊዜ ተጠቃሚ እንዲሆን ያሰበውን ሰው ያለጥርጥር የሚያሳይ ከሆነ የተጠቃሚውን መለያ /በቤተሰብነት፣ በሙያው፣ በማሕበራዊ ግንኙነት/ መጥቀስ በቂ ነው። ተጠቃሚው ሰው ተለይቶ ሊታወቅ መቻሉ ብቻ ይበቃል። ስለዚህ መድን ለገባው ሰው ሚስት ጥቅም፣ እንዲያውም ከዚያም አልፎ ለባለ መድኑ ባለቤት ጥቅም፣ ሲባል የተደረገ ውል ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አለው"።[8]

ቁ. 701/2/ ተጠቃሚውን አጠቃላይ በሆኑ ቃላት ከመወሰን ጋር የሚያያዙ ሌሎች ጥያቄዎችንም ይመለከታል። ለምሳሌ "ሚስት" ወይም "ባለቤት" የሚሉ ቃላት በሚጠቀሙበት ጊዜ የሚነሣው ጥያቄ የትኛዋ? ተዋዋዩ ውሉን በተዋዋለበት ጊዜ የነበረችው ሕጋዊ ሚስቱ ወይስ በሚሞትበት ጊዜ አብራው የነበረችው ሕጋዊ ሚስት? የሚለው ነው። ተዋዋዩ ውሉን በተዋዋለበት ጊዜ ያላገባ ከነበረና በኋላ ካገባ ቁ. 701/2/ ግልፅ ይሆናል። ይህቺ ዓይነቷ ሚስትም ትክክለኛዋ ተጠቃሚ ትሆናለች።

ተዋዋዩ ውሉን በተዋዋለበት ጊዜ "ተ"ን አግብቶ ከነበረና በኋላ እሷን ፈትቶ "ሞ"ን አግብቶ እያለ በሚሞትበት ዓይነት ሁኔታ ግን የሕጉ ቋንቋ በሚፈለገው መጠን ግልፅ አይሆንም። ያም እንኳን ቢሆን ዕውቅና መስጠት የተፈለገው "ፖሊሲው ከተፈረመ በኋላ" የተደረገውን ጋብቻ ይመስላል። ይህ አቋም ለፖሊሲው መሠረት የሆነውን ምክንያት በመጥቀስ ሊደገፍ ይችላል። ይህም ምክንያት በአብዛኛው አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ ለቅርብ ቤተሰቡ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማቅረብ የሚለው ነው።

ተጨማሪ ድጋፍ አሁንም እንደገና ከፈረንሣይ ሕግ ሊገኝ ይችላል። እዚያም "ጋብቻው በፈረሰ ጊዜ /በሞት ወይም በፍቺ/ ቀድሞ የነበረው የተጠቃሚው አጠቃቀስ ስሌት ወዲያውኑ ለሁለተኛዋ ሚስት ወይም ለሁለተኛው ባል ጥቅም ይውላል" ተብሎ ተወስኖአል።[9]

"ልጆችን በተመለከተ ይህ የያዝነው ሕግ ግልፅ ነው፤ ከውሉ መፈረም በፊት የተወለዱት ብቻ ሳይሆኑ ከዚያ በኋላ የተወለዱት ልጆችም በተጠቃሚነት ተጠቃለዋል።

"ተጠቃሚዎቹ በመለያቸው የተጠቀሱ ከሆኑ ባለኢንሹራንሱ በሚሞትበት ጊዜ ጥቅሙ ውሉ ሲደረግ የተወለዱትን ወይም የተፀነሱትን ልጆች ወይም የልጅ ልጆች ብቻ ሳይሆን ገና ሊወለዱ ያሉትን ጭምር ያጠቃልላል።[10]

---

8 ይህንኑ መጽሐፍ ገጽ 29 ይመለከቷል።

10 እዚያው ቦታ ይመለከቷል።

## ማጠቃለያ

ለሞት ጊዜ የሚደረግ የሕይወት ኢንሹራንስ ቀዳሚ ዓላማ የተዋዋዩ የቅርብ ቤተሰብ አባላት ከድንገተኛ ችግር ለመከላከል ነው የሚለው እምነት አለማአቀፋዊ ለማለት በሚያስደፍር ደረጃ ሰፍኖባቸው የነበሩ ጊዜአት ነበሩ። በጊዜው የነበሩት ማሕበራዊና ምጣኔ ሐብታዊ ሁኔታዎችም ይህን አመለካከት የሚያጠናክር ነበሩ። ከነዚህም ሁኔታዎች ውስጥ ዋናው በአብዛኛው በዚያ ጊዜ ወንዱ ብቸኛው የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ የነበረ መሆኑና የእሱ መሞት ማለትም በተጋቢዋ ላይ የግድ የማይቀር ምጣኔ ሐብታዊ ውድቀት ማስከተሉ ነው። በዚህ ምክንያት በዚያ ጊዜ ሰዎች የሕይወት ኢንሹራንስ የሚገቡት እንዲህ ዓይነት ውድቀቶችን ለመቋቋም ሲሉ ነበር። ይህ ሁኔታ የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲን ከተዋዋዩ የቅርብ ቤተሰብ ጋር አንድ አድርጎ መመልከትን አስከተለ። የዚህ መሰሉ ሁኔታ በበኩሉ በብዙ ቀደምት የአውሮፓ አገሮች ሕጎች ውስጥ ተንፀባርቋል።

ሥልጣኔ እየጨመረ ሲመጣ ነገሮች ሁሉ እመርታዊ ለውጥ አድርገዋል። በመጀመሪያ ደረጃ ቢያንስ ቢያንስ በብዙዎቹ ዘመናዊ የኢኮኖሚ መስኮች ከቤተሰብ አባላት ውስጥ የሰውየው ብቸኛ የገቢ ምንጭነት አክትሟል። ሁለተኛ ደግሞ ብዙ አገሮች ብዙ ዓይነት የማሕበራዊ ደሕንነት መጠበቂያ ዘዴዎችን (Social Security Schemes) የቀየሱ በመሆኑ የአንድ የቤተሰብ ኃላፊ መሞት የቤተሰቡ አባላት ለችግር ለመጋለጣቸው ጠቋሚ ሆኖ መታየቱ የቀረ ሆኗል። ስለዚህ እነዚህ ለውጦች በተከሰቱባቸው አገሮች ውስጥ የሕይወት ኢንሹራንስ መግባትን ቀዳሚ ዓላማ ለቤተሰብ መሠረታዊ ችግሮች ማቃለያ እንዲሆን አድርጎ መውሰዱ ቀርቷል።

በዚህ መሐከል የንግዱ ዓለም ለሕይወት ኢንሹራንስ ሌላ ጠቀሜታ አግኝቶለታል። ለምሳሌ የአንድ ሌላ ሰውን ግዴታ ለመወጣት ዋስትና ለመስጠት እጅግ በጣም የተሻለው ዘዴ መሆኑ ታውቋል።

ከዚያም፣ ምንም እንኳን በጣም ዘግይቶ ቢሆንም ቅሉ ሕጉ ከተለወጠው ሁኔታ ዘንድ መድረስ ነበረበት። ይህም ማለት በብዙ ያደጉ አገሮች ለተዋዋዩ ነፃ ፍላጎት ትልቅ ትኩረት እንደመስጠት ተደርጎ ነበር የተወሰደው።

ከላይ ኾኖሬ እንዳሉትም የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ አወሳሰንን በተመለከተ ኢትዮጵያ የተቀበለችው ይህን መሰሉን ልቅ አቋም ነበር።

በርግጥ ማሕበራዊና ምጣኔ ሐብታዊ ሁኔታዋ ከአውሮፓ እጅግ በምትለይ አገር ውስጥ ይህን ዓይነቱን ፖሊሲ መቀበሉ ምን ያህል አዋቂነት እንደሆነ ሊያጠያይቅ የሚችል ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያ ፖሊሲ ነዳፊዎችም ይህን እውነታ ሳይገነዘቡ ቀርተው አልነበረም። ሆኖም ኢትዮጵያን ወደ ሰለጠነው ዓለም ደረጃ ለማድረስ ዘመናዊ ሕጎች ሊጠቀሙ ይችላሉ የሚል እምነት ነበራቸው። ከዚህም በላይ ዘመናዊ የኢንሹራንስ ሕግ በወቅቱ በተነደፈው የአገሪቱ የዕድገት ፖሊሲ ውስጥ ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት የነበረውን የውጪ ካፒታል ለመሳብ እንደሚያገለግልም ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ በውሳጣዊ ሁኔታዎችና ከውጪ መጥቶ በተቀዳው ሕግ መካከል መፈጠሩ አይቀሬ የነበረውን የውጥረት ጊዜ የፖሊሲው ነዳፊዎች ተቀብለውት የነበረ መሆን አለበት። ከላይ የጠቀስናቸው የሁለት ፍ/ቤቶች ውሳኔዎችም በመጠኑ የዚህ ውጤት ነፀብራቆች ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ዳኞች ሊያነሷቸው ከሚገቡ ብዙ ጥያቄዎች መካከል የተዋዋዩን ፍላጎት የበላይነት በሚጠብቅ ሕግ ውስጥ የባል ወይም የሚስትን ጥቅሞች እንዴት መጠበቅ ይቻላል? የሚለው ነው።

አሜሪካን፣ ፈረንሳይንና የቀድሞዋን ምዕራብ ጀርመን ጨምሮ ልቅ የሆነ የኢንሹራንስ ሕግ ያላቸው ብዙ አገሮች በሕይወት ላለው ባል ወይም ሚስት ጥቅም ይበጃል ተብሎ በሚታመን ጊዜ ይህን ጥቅም መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን ዕውቅና ይሰጣሉ። ምንም እንኳን ሕጎቻቸው ተዋዋዩ ተጠቃሚውን ለመወሰን ባለው ነፃነት ውስጥ ጣልቃ መግባት እንደሚቻል በግልፅ ባይፈቅዱም ፍ/ቤቶቻቸው ግን በብዙ አጋጣሚዎች የተዋዋዮችን ፍላጎት ውድቅ አድርገዋል።

በብዙ የምዕራብ አገሮች በጣም የተለመደው ጉዳይ አንድ ያገባ ሰው ቅምጡን በተጠቃሚነት የመጥቀሱ ሁኔታ ነው። ፍ/ቤቶቹም ይህን መሰሉን አጠቃቀስ በተደጋጋሚ ለሕሊና ተፃራሪ /contra bones mores/ ነው በማለት በተጠቃሚነት ባትጠቀስም እንኳን የኢንሹራንሱን ጥቅም ለሚስቱ ይሰጥ እያሉ ሲፈርዱ ይታያል።

በሕይወት መድን ውል ተጠቃሚን ስለመሰየም

በዚህ መሠረት የሕይወት ኢንሹራንስ ጥቅም ለቅርብ ቤተሰቡ ብቻ መስጠት አለበት ብለው በሚያምኑና ለተዋዋዩ ፍላጎት የበላይነትን መስጠት ላይ በሚያተኩሩ መካከል ያለውን ክፍተት በቃ ለመሙላት ይህ አቀራረብ የተሻለ ማስታረቂያ ይመስላል። አቀራረቡ ሦስተኛ ሰውን ፍፁም ሕጋዊ ለሆኑ ምክንያቶች ተጠቃሚ አድርጎ ለሚጠቅስ ተዋዋይ ፍላጎቱን ሲያውቅና ሙሉ ውጤት ሲሰጥ ተጠቃሚው የተጠቀሰው በሕሊናና ለቅን ልቡና ተቃራኒ በሆነ ምክንያት ከሆነ ደግሞ የተዋዋዩን ፍላጎት ማፍረስ ያስችላል።

ነገር ግን ተዋዋዩ ሦስተኛ ሰውን በተጠቃሚነት የመጥቀስ መብቱን ስለመልካም ፀባይ ካለን አመለካከት ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ሲጠቀምበት ወይም ፍ/ቤቱ የተደረገ የማታለል ድርጊት አለ ብሎ በሚያምንበት ሁኔታ ውስጥ በሚወድቅበት ጊዜ ይህ አማራጭ ለኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች እንደማይኖራቸው ይታመናል። የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ልዩ ውል እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 12 ውስጥ በሚገኙ አጠቃላይ ሕጎች የሚታይ መሆኑ እውነት ነው። ስለዚህ ፍ/ቤቱ ከሕሊና ተቃራኒ የሆነ ነገር አለ ብሎ ባመነ ጊዜ በዚህ ሕግ መሠረት የኢንሹራንስ ውሉን ሊያፈርሰው ይችላል። በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ ግን የማፍረስ ውጤት በርትዕ ላይ ተመሥርተው የሚሰጡ የአሜሪካና ያውሮፓ ፍ/ቤቶች ውሳኔዎች ወደሚደርሱበት መፍትሄ አይወስድም፤ ለምሳሌ እነዚህ- ፍ/ቤቶች ተዋዋዩ በጠቀሰው ተጠቃሚ ቦታ ተዋዋዩ ያልጠቀሰውን ሰው ይተካሉ።

በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ ግን የማፍረስ ውጤት ተዋዋዮችን ማለትም ኢንሹራንስ የገባውን ሰውና ኢንሹራንስ የሰጠውን ካምፓኒ ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ ነው። ይህም በውጤቱ ሁለት ነገሮችን ማለት ነው፤

አንደኛ ኢንሹራንስ የገባው ሰው በውሉ ውስጥ እንደሚከፈል የተገለፀውን ያህል ገንዘብ ሳይሆን ለኢንሹራንስ መግቢያ የከፈለውን ገንዘብ /ምናልባትም ወለዱን ጨምሮ/ በሙሉ እንዲመለስለት ይደረጋል። በሁለቱ ገንዘቦች መካከል ከፍተኛ የመጠን ልዩነት ሊኖር መቻሉ ግልፅ ነው።

ሁለተኛ ይህ ጥያቄ የሚነሳው ተዋዋዩ ከሞተ በኋላ እንደመሆኑ ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ በመደረጉ ምክንያት የሚገኘው ገንዘብ የሚሰጠው በርትዕ ወይም በበጎ ሕሊና

ላይ ተመሥርተው ተጠቃሚ መሆን ለሚገባው የተወሰነ ሰው ሳይሆን ለሟቹ ውርስ /estate/ ነው።

ስለዚህ ፍርድ ቤቱ ውሉን በማፍረሱ ለተጎዳው ክፍል ፍትሕ የመሥራት ዓላማውን ሳያሳካ የውሉን ፍሬ ነገር ብቻ ያጠፋዋል ማለት ነው። ወደ ተፈለገው ግብ ሊያደርስ የሚችል የሚመስለው መንገድ የውሉን ይዘት መለወጥ ነው፤ ይህም በውሉ የተጠቀሰውን ተጠቃሚ ባልተጠቀሰ ተጠቃሚ መተካቱ የሚሰጠው ትርጉም ነው። "የውል ነፃነት" በሚለው መርሕ ላይ በጠንካራ ሁኔታ የተመሠረተው የኢትዮጵያ የውል ሕግ በሕጉ ላይ ተገልጾ የተመለከተ ካልሆነ በቀር ዳኞች ርትዕን ምክንያት በማድረግ ውሉን ለማሻሻልም ሆነ ለመለወጥ አይችሉም፤ /ቁ. 1763/ በማለት አጠንክሮ ይናገራል። በጠባቡ የተወሰኑትና ከዚህ መርህ የሚያፈነግጡት ሕጎች /ቁ. 1766-1770/ እንኳን ቢሆኑ አንድን ተጠቃሚ በሌላ እስከመተካት ደረጃ የሚያደርስ ለውጥ በፍፁም አይፈቅዱም። ከዚህ አወንታ አንፃር ሃፍሬ "በጣም ልቅ መፍትሄ" መርጫለሁ ማለታቸው የተሟላ ስሜት ይሰጣል።

---

11 ያልተገባብ ስለመበልፀግ /የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 688/ ያለው ሕግ በመተቀስ ባል ወይም ሚስት "ያገኙትም ወገን የግል ሐብት በሌላኛው የግል ሐብት ወይም በጋራ ሐብት ላይ ያስገባብ መብዛቱን ማረጋገጥ ከቻለ" ኪሣራ እንዲከፈለው ይደረጋል የሚል አቀጋቢ ያልሆነ መፍትሄ ማግኘት ይቻላል።